የፌየርፋክስ ካውንቲ

የግብር አስተዳደር መመሪያ (DEPARTMENT OF TAX ADMINISTRATION)



# የ2025 የሪል ስቴት የግብር ግምት መረጃ

## መታወቅ ያለባቸው ዋና ዋና ቀናት

**ሚያዚያ 1** በግብር ግመታዎ ላይ አስተዳደራዊ ይግባኝ የሚያቀርቡበት የመጨረሻ ቀን

**ግንቦት 1** ለግብር እፎይታ ማመልከቻ ማብቂያ ቀነ ገደብ

**ግንቦት 13** የኃላፊዎች ቦርድ አፊሴላዊ የሪል ስቴት ግብር ተመኖችን የሚወስንበት

***ሰኔ 2** በግብር ግምትዎ ላይ ለማመጣጠኛ ቦርድ ይግባኝ የሚያቀርቡበት የመጨረሻ ቀን * **ሰኔ 1** ቀን እሁድ ቀን ስለሆነ ተራዝሟል

**ሰኔ መጨረሻ** የሪል ስቴት ግብር ክፍያዎች የመጀመሪያ ዙር ክፍያ የሚላክበት ቀን

**ሰኔ 28** የሪል ስቴት ግብር ክፍያዎች: ነኛ ዙር ክፍያ የሚከፈልበት ቀን

**ሕዳር መጀመሪያ** የሪል ስቴት ግብር ክፍያዎች ሁለተኛ ዙር ክፍያ የሚላክበት

**ታህሳስ 5** የሪል ስቴት ግብር ክፍያዎች: 2ኛ ዙር ክፍያ የሚከፈልበት ቀን

በሕግ የፌየርፋክስ ካውንቲ በጥር ነ ቀን ሁሉም ሪል ስቴቶች ላይ በ100% ፍትሀዊ የገበያ ዋጋቸው ግብር መገመት አለበት።

**የመኖሪያ ንብረቶች**

በ2024፣ የ30-ዓመት ቋሚ የቤት ብድር (ሞርጌጅ) ተመኖች የተወሰነ መዋዠቅ ያሳዩ ቢሆንም፣ በአጠቃላይ ከፍ ያለ ሆኖ ቆይቷል፣ ይህም በአማካይ ከ7.0% ትንሽ አነስ ያለ ነበር። የእቃዎች የክምችት መጠን ከፍተኛ መሻሻል ያሳየ ሲሆን፣ የሽያጭ መጠን ደግሞ መጠነኛ ጭማሪ አሳይቷል። በቅርብ በታየው የሽያጭ ሁኔታ ላይ በመመስረት፣ የቤት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ የጨመረ ሲሆን፣ የጭማሪው መጠን በ 2023 ከነበረው ከፍ ያለ ነው።

**የንግድ ንብረቶች**

ከፍተኛ የሆነ ክፍት የስራ መደቦች በመኖራቸው እና የዕዳ ግዴታዎችን ለመወጣት ባለባቸው ችግሮች ምክንያት የቢሮ ገበያው ያለበት ችግር ቀጥሏል። ከ2024 የግብር ዘመን ጋር ሲነጻጸሩ የቢሮ ዋጋዎች በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሰዋል። የችርቻሮ፣ የባለብዙ ቤተሰብ፣ እና የኢንዱስትሪ ንብረቶች መጠነኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ አሳይተዋል።

- በጀርባው ይመልከቱ -



# የግብር ግምትዎን መረዳት

የንብረት ዝርዝሮችዎን እና የግብር ግምቱን ለመወሰን የታዩ ተነጻጻሪ ሽያጮችን ከwww.fairfaxcounty.gov/taxes/real-estate ላይ በመመልከት ይጀምሩ።

በሚከተሉት ምክንያቶች በንብረትዎ ግምት ላይ ካልተስማሙ:

- ከፍትሀዊ የገበያ ዋጋ በላይ ሆኖ በመገመቱ፣
- ከተመሳሳይ ንብረቶች ጋር ሲነጻጸር ወጥነት/ተመሳሳይነት ባለው መልኩ ባለመገመቱ፣ እና/ወይም
- የንብረት ምዝገባዎን በተመለከተ የተሳሳተ በመሆኑ

ስለ ጥያቄዎችዎ ወይም ማወቅ የሚፈልጓቸው ጉዳዮች በተመለከተ ከካውንቲ ገምጋሚ ጋር እንዲወያዩ እንመክርዎታለን።

ይግባኝዎን እስከ **ሚያዚያ 1**፣ ድረስ ለአስተራደራዊ ይግባኝ ሊያቀርቡ፣ ወይም እስከ **ሰኔ 2**ድረስ ለማመጣጠኛ ቦርድ ሊያቀርቡ ይችላሉ።* **ሰኔ 1** ቀን እሁድ ቀን ስለሆነ ተራዝሟል። ይግባኝን ለማመጣጠኛ ቦርድ ከማስመዝገብ በፊት በመጀመሪያ ለአስተዳደራዊ ይግባኝ ማስመዝገብ ይመከራል።

ወደ www.fairfaxcounty.gov/taxes/real-estate በመግባት ወይም በስልክ ቁጥር 703-222-8234, TTY 711 በመደወል ተጨማሪ ይወቁ እንዲሁም የይግባኝ ቅጾችን ያግኙ።

የፌየርፋክስ ካውንቲ የግብር አስተዳደር መመሪያ፣ የሪልስቴት ምድብ
(Fairfax County Department of Tax Administration, Real Estate Division)
12000 Government Center Parkway, Suite 357
Fairfax, VA 22035

ኢሜይል፥ dtared@fairfaxcounty.gov
ስልክ፥ 703-222-8234, TTY 711 (ለእንግሊዘኛ/ስፓኛል)
ሰኞ - አርብ ከ 8 a.m. እስከ 4:30 p.m.

## ቀጠሮ በማስያዝዎ ላይ እርዳታ ያግኙ

በስልክ ወይም በቪዲዮ እርዳታ ለማግኘት ቀጠሮ ያስይዙ። ቀጠሮ ለማስያዝ QR ኮዱን ስካን ያድርጉ ወይም www.fairfaxcounty.gov/taxes/appointments ን ይጎብኙ።



ይህን መረጃ በአማራጭ ፎርማት ለመጠየቅ የግብር አስተዳደር መምሪያን (Dept. of Tax Administration) በስልክ ቁጥር 703-222-8234, TTY 711 ያነጋግሩ።
የፌየርፋክስ ካውንቲ (Fairfax County), Va. ዕትም። የካቲት 2025።